# «አቶ» ዲያብሎስ

ለወትሮው በስንኞች ስሜቴን መግለጽ ይቀናኝ ነበር፤ አሁን የምጽፍበት ጉዳይ ግን ለስሜቴም ለብዕሬም የከበደና የተወሳሰበ ሆነ መሰለኝ ግጥም ለመጻፍ አላነሣሣኝም። በስንኝ መልክ ይሁንም አይሁንም ብቻ ጉዳዩን «ያገባኛል» ለሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በዚህች ጽሁፍ በኩል ላቀርብ ወደድሁ።

ዘመኑ የተራቀቀ የቴክኖሎጂ ዘመን ሆነና ከአንደበትም ከብዕርም የሚፈልቁ ቃላት በዓለም ዙሪያ ለመዳረስ የሚፈጅባቸው ጊዜ በሰኮንዶች ብቻ የሚቆጠር ሆኖአል። በእርግጥ እጅግ የሚያስደንቅ የሰው ልጅ የጥበብ ደረጃ ላይ ደርሰን የጥበቡ ተጠቃሚዎች ለመሆን በመታደላችን ደስ ሊለን ይገባል። ነገር ግን ደግ ቃላት እንዳሉ ሁሉ ክፉ ቃላትም ሞልተዋልና ደጉም ክፉውም ቃላት ቴክኖሎጂውን እኩል ተጠቅመው በእኩል ፍጥነት ዓለምን ይዞራሉ። ለዚህም ነው በዚህ ባለንበት የፈተና ዘመን ከአንደበታችንም ሆነ ከብዕራችን የሚፈልቁ ቃላት ማንነታችንን የሚያጎለብቱ እንጂ የማያዳክሙ፥ የሃይማኖትና የታሪክ ቅርሶቻችንን የሚያከብሩ እንጂ የማያረክሱ፥ መንፈሣዊና ዓለማዊ ሕይወታችንን በይበልጥ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የሚያስተሳስሩ እንጂ የማይነጣጥሉ መሆን የሚጠበቅባቸው። ለኢትዮጵያ አንድነት የቆምን፥ ለኢትዮጵያዊ ማንነታችን የምንቆረቆር ከሆንን ዛሬ እንደቀልድ የምንወረውረው ቃልና የምንለጥፈው ስያሜ ለረጅም ጊዜ ማንነታችን ላይ ተጣብቆ፥ እምነታችንን አቆሽሾ፥ የሌሎችም መሳለቂያ አድርጎን ሊያልፍ እንደሚችል አስቀድመን መገንዘብ ይኖርብናል። ሃይማኖት ቀልድ አይደለም፤ በሕዝበ ክርስቲያኑ፥ በካሕናቱ፥ በአምልኮ ሥርዐቱ ላይ ያነጣጠረ አጉል ቀልድ የሚያስቀን ከሆነ ለምን እንደሳቅን ቆም ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል። በአገርና በወገንም ጉዳይ ላይ እንዲሁ። በተለይም እንደዛሬው አገር የሚገነጥል፥ ሕዝብ የሚከፋፍል፥ ኢትዮጵያዊነትን የሚያዳክም ሕገወጥ መንግሥት በላያችን ላይ በተጫነበት አስቸጋሪ ወቅት ማንነታችን ላይ ጠባሳ የሚጥል ሥራ እየሠራን ሳናውቀው የዓላማው ተባባሪ እንዳንሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

«አባ ዲያብሎስ» የሚል ስያሜ በአሁኑ ጊዜ በመንበሩ ላይ ለተቀመጡት ፓትርያርክ ተሰጥቶ ተመልክቻለሁ፤ እኔ ግን በስያሜው አልስማማም። ፓትርያርኩ በእግዚአብሔርም፥ በሕዝብም፥ በታሪክም ፊት የሚያስጠይቃቸው ብዙ በደሎችን እንደፈጸሙ ሰምተናል። ሕዝብ በግፈኛው የወያኔ መንግሥት በጭካኔ ሲገደል፥ ድምፁ ሲታፈን፥ ያለአግባብ ሲታሰር፥ የመረጣቸው እውነተኛ መሪዎቹ በወያኔ ማናለብኝነት ወደ ወህኒ ሲወረወሩ ፓትርያርኩ ድምፃቸውን አለማሰማታቸው ብዙዎቻችንን አስቆጥቶናል። ሰማእታት ሆነው እንዳለፉት እንደ ቀድሞዎቹ የሃይማኖት መሪዎች ለእውነት፥ ስለእውነት ለመቆም ባለመቻላቸውም በእኒሁ በዛሬው ፓትርያርክ ብዙዎቻችን አዝነንባቸዋል። ሌላው ሌላው ሳይጨመር፥ ክርስትና በተነሣሁበት፥ ከህጻንነት እስከ ዕውቀት የሃይማኖቴን ሥርዐት እየተመለከትኩ ባደግሁበት ባዲሳባው የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ ፓትርያርኩ በተገኙበት ተፈጸመ የተባለውን ግፍ ባሰብኩ ቁጥር መንፈሴ ይረበሻል። ነገር ግን ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ፓትርያርኩ ላይ ያለኝን ቅሬታ ለማሳየት ብዬ ለዲያብሎስ «አባ» የሚል ሹመት ለመስጠት አልደፍርም።

አንድ መዘንጋት የሌለበት ሃቅ አለ፤ አገርን ለአደጋ አጋልጠው፥ ሕዝብንም በድለውና ከፋፍለው ሥልጣን ላይ የተቀመጡት ግፈኞች፥ ከሃዲዎች፥ ገንጣዮች ያልፋሉ። የማያልፉትና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት ኢትዮጵያዊ እሴቶች ግን ሁልጊዜም ከኢትዮጵያውያን ጋር ይኖራሉ። እንደወያኔ ዓይነት እኩይ ቡድን በመጣ ቁጥር እነዚህ ኢትዮጵያዊ እሴቶች መጎሳቆላቸው፥ መጠቃታቸውና ችላ መባላቸው አይቀርም፤ ነገር ግን ጽኑ መሠረት አላቸውና አይጠፉም። ፓትርያርኩ ይሄዳሉ፤ «አባ እገሌ» እያልን የምንጠራቸው እውነተኛ አባቶች ግን ሁልጊዜም በመካከላችን ይኖራሉ። እነዚህን አባቶች ለመጥራት የምንጠቀምበትን «አባ» በግዴለሽነት የትም ልንወረውረው፥ ለዲያብሎስም አሳልፈን ልንሰጠው አይገባም። ለዚህም ነው የፓትርያርኩን ተግባር አጥብቄ እንደምቃወመው ሁሉ «አባ ዲያብሎስ» የሚለውንም ስያሜ የማልደግፈው።

«አባ ዲያብሎስ» መነሻ ሆኖኝ ይህቺን ጽሁፍ ጀመርኩ እንጂ ሌሎችም የበለጠ ሊያሳስቡን የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉ አልዘነጋሁም። ኢትዮጵያ ከተጫኑባት አያሌ ችግሮች አንጻር የ«አባ ዲያብሎስ» ጉዳይ እጅግ በጣም ኢምንት ሆኖ ሊታይ ይችላል። ቢሆንም የማንነት መሸርሸር ከጥቃቅን ሥነ ልቡናዊ ሰለባዎች ይጀምራልና ሕዝብ ተሳስቦና ተቻችሎ የኖረባት አገራችን ብርቅዬ እሴቶችዋ በክብር ተጠብቀው እንዲቆዩ ሁላችንም የየበኩላችንን ድርሻ

**የመወጣት ዜጋዊ ግዴታ አለብን። የምንጽፈውም ሆነ የምንናገረው ቃል ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎለብትና ትውልድን የሚያንጽ እንዲሆን ኢትዮጵያውያን ሁሉ በቀና አመለካከት ላይ የተመሠረተ የማያቋዋርጥ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።**

**መቼም ችግሮቻችን ሌሎች ችግሮች እየወለዱ በተደጋጋሚ መከራችንን ማብዛታቸው አልቀረምና አሁን ደግሞ ለዲያብሎስ ሌላ ሹመት መፈለግ ሊኖርብን ነው፤ «አባ» የሚለው ስያሜ ፈጽሞ የእርሱ አይደለምና። ለጊዜው ግን ለምን ወደ ብዙዎቻችን ተራ አውርደነው «አቶ» ዲያብሎስ፥ ወይም «ዶክተር» ዲያብሎስ፥ ወይም «ሚስተር» ዲያብሎስ እያልን አንጠራውም? . . . ለነገሩ ለእኛ ለዘመናውያኑ ሳይቀርበን ይቀራል?**

---

ቴዎድሮስ አበበ
July 18, 2006